የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የጤና ፖሊሲ

2007

# ይዘት

- የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት የጤና ፖሊሲ
- የጤናው ፖሊሲ ክለሳ አስፈላጊነት እና ቀጣይ የጤናው ዘርፍ ሁኔታ
- ራዕይ፣ ተልዕኮ
- የአዲሱ ፖሊሲ ግብ እና ዓላመዎች
- የአዲሱ ፖሊሲ  የፖሊሲ  አቅጣጫዎችና  ስልቶች
- የአዲሱ ፖሊሲ አተገባበር

# የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት የጤና ፖሊሲ

- 1986 ሽግግር መንግስት ጊዜ የተዘጋጀ
- የአገሪቱን የጤና አገልግሎት ሽፋን ከነበረበት እጅግ አነስተኛና ኢፍትሐዊ ደረጃ ለማሻሻል እና የሕዝቡን የጤንነት ሁኔታ ለመቀየር የሚያስችል ሆኖ የተዘጋጀ
- በዋና ዋና ለጤና ጠንቅ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የሕብረተሰቡን ግንዛቤ፤ እምነት፤ ባህሪና ድርጊት ለመለወጥና ብዙዎቹን የጤና ችግሮች ለማስወገድ፡
  - በተለይም ደግሞ አብዛኛውን የገጠሩን ህብረተሰብ፣ አርብቶ አደሩንና ደሃ ከተሜውን ታሳቢ ያደረገ
  - በሽታን አስቀድሞ በመከላከል ላይ ዋናው አማራጭ ያደረገ ነበር።

# የኢትዮጵያ ሽግግር …

- የጤና ፖሊሲው ትግበራ፡
  - የጤና አገልግሎት አሰጣጥ እርከኖች በማዋቀርና ያልተማከለ አመራር እንዲኖረው በማድረግ ተጀመረ
  - የ20 ዓመት የጤናው ዘርፍ የልማት መርሐ ግብር በመቅረፅና በአራት ተከታታይ ዙሮች በማዘጋጀት መርሐግብሮቹ ተግባራዊ ሲደረጉ ቆይቷል
  - በ1997 ዓ.ም. የአገሪቱን አስፈላጊ የጤና አገልግሎት ፓኬጅ (Essential Health Service Package) በማዘጋጀት አገልግሎቱን የማስፋት ሰፊ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል
  - የአገልግሎት አሰጣጡ የስራ ሂደት በተቀናጀና በተቀላጠፈ መልኩ ተጠቃሚውን ለማርካት እንዲቻል የአገልግሎት ሥርዓት መልሶ ግንባታ ጥናት /Business Process Reenginering/ በማካሄድ የጤናው ዘርፍ በሦስት ዋናዋና ክፍሎች ማለትም በአገልግሎት ሰጪ፤ አገልግሎት ተቆጣጣሪ እና አገልግሎት ገዢ እይታ በማዳራጀት የሀገሪቱን የጤና አገልግሎት ለማሻሻል ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

# የጤናው ፖሊሲ ክለሳ አስፈላጊነት እና ቀጣይ የጤናው ዘርፍ ሁኔታ

- በርካታ አገራዊ፣ አህጉራዊ እና አለምአቀፋዊ ሁናቴዎች በመለዋወጣቸው
  - የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት፣ የስነ ህዝብ ሁኔታዎችን፣ የከተማዎችና የኢንዱስትሪ መስፋፋትን፣ ግሎባላይዜሽን፣ የአየር ጠባይ ለውጥና የቴክኖሎጂ ለውጦችን፣
- ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ስርጭት እና በተለያዩ ምክንያት የሚያጋጥሙ አደጋዎች በጤና አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ጣምራ ጫና ከግንዛቤ በማስገባት እነዚህን ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲሆን፤
- የህዝቦችን ብልጽግናና የአገሪቱን እድገት እውን የሚያደርግ ሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊ በማድረግ የበለጸገች አገር ለመፍጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ፤
  - የጤናው  ዘርፍ የራሱን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት እና
  - የኢኮኖሚ እድገቱ ውጤት የዜጎችን ጤናና ደህንነት ወደ ተሻለ ደረጃ ማድረሱን ለማረጋገጥ እንዲያስችላል፡፡

# አዲሱ የተከለሰው የጤና ፖሊሲ

# ራዕይ፡

# ጤናማ፣ ምርታማና የበለጸገ ኅብረተሰብ ተፈጥሮ ማየት ነው፡፡

## ተልዕኮ፡

ጥራቱን የጠበቀ፣ ፍትሐዊና ተደራሽ የሆነ የጤና ማበልጸግ፣ በሽታ መከላከል፣ የፈውስ ህክምናና የተሃድሶ የጤና አገልግሎት በመስጠትና በመቆጣጠር

# ግብ፡

- *ሁሉአቀፍ የጤና አገልገሎት ተደራሽ በማድረግ እና ዜጎች በጤና ችግር ምክንያት ለኢኮኖሚ ቀውስ በማይዳርግ መልኩ አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፤ እንዲሁም ጤናን በሁሉም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አጠቃላይ የልማት ፖሊሲዎች በማካተት የኢትዮጵያውያንን ጤናና ደህንነት*

# ዓላማዎች

- *የጤና ፖሊሲው አጠቃላይ አላማ ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት በጤና ውጤታቸው ከላቁት ጋር ተመጣጣኝ የጤና ሁኔታ እንዲኖራት ማስቻል ሲሆን ዝርዝር አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡*
  - *ጥራት ያለው ሁሉአቀፍ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ማረጋገጥ*
  - *መከላከል በሚቻሉ ምክንያቶች የሚደርሱ የእናቶችና ህጻናት ሞት መግታት፤*
  - *ጤና ማበልጸግና በሽታ መከላከል ማዕከል በማድረግ ተላላፊ፣ ተላላፊ ያልሆኑና በተለያዩ አደጋዎች ሳቢያ የሚደርሱ ህመምና ሞትን መቀነስ፤*
  - *አማካኝ የመኖር እድሜ ጣርያ ማሳደግ*

# እሴቶች

1. የማህበረሰብ ጥቅሞች ማስቀደም
2. ቅንነት፣ ታማኝነትና ሐቀኝነት
3. ግልፅነት፣ ተጠያቂነትና ምስጢር መጠበቅ
4. አድልዎ አለመፈፀም
5. ሕግን አክባሪነት
6. አርአያነት
7. መደጋገፍ
8. ለሙያዊ ሥነ-ምግባር ተገዢ መሆን
9. ለለውጥ ዝግጁነት
10. ርህራሄ

# መርሆዎች

- ትኩረት ለጤና ማበልፀግና በሽታ መከላከል
- ሁሉአቀፍ ተደራሽነት
- የማህበረሰብ ባለቤትነት
- ትኩረት ለመሠረታዊ ጤና አገልግሎት
- ራስን መቻል
- ህሙማንን/ታካሚ/ተጠቃሚ ማዕከል ያደረገ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት
- ፍትሀዊነት
- መልካም አስተዳዳር
- የፆታ እኩለነት
- እናቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ተኮር
- አሳታፊ አጋርነት
- ዘወትር የሚማርና ለውጥን የሚቀበል የጤና አገልግሎት ስርዓት
- ሙያዊ ግዴታና ሥነ-ምግባር
- ዘርፈ ብዙ ትብብር

# የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስልቶች

1. የማህበረሰብ ባለቤትነት ማረጋገጥ
2. ፍትሃዊ  እና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት መስጠት
3. የህብረተሰብ ጤና አደጋዎችንና መሰል ክስተቶችን የሚቋቋምና ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ የጤና ሥርዓትን ማጠናከር
4. የጤናው ዘርፍ የሰው ሀብት ልማት ማሻሻል
5. የጤና መረጃ፣ ጥናትና ምርምር እና የእውቀት አስተዳደርን ማጎልበት

# የፖሊሲ አቅጣጫዎችና ስልቶች

6. የመድሀኒት አቅርቦትና የህክምና ቴክኖሎጂን ማሻሻል
7. የጤና ቁጥጥር ስርዓት ማጠናከር
8. የጤና ክብካቤ ገንዘብ ምንጭ እና አጠቃቀም ማጎልበት
9. የጤና ስርዓት አመራርና አስተዳደር ማጠናከር
10. የባህል ህክምና ማሻሻል
11. ጤና በሁሉም ፖሊሲዎች

# የፖሊሲው አተገባበር

1. **ተቋማዊ አቅምን ማጠናከር**
2. **የሕግ ማእቀፎችን ማበጀትና የማስፈጸሚያ ስልቶችን ማጎልበት**
3. **ስትራቴጂክ እቅዶችን፣ ፍኖተ ካርታዎችንና የአተገባበር መመሪያዎችን እንደየአስፈላጊነቱ በመንደፍ ወደ ተግባር መመንዘር**
4. **የክትትልና ግምገማ**
5. **የመዋዕለ-ንዋይ (የፋይናንስ) አቅርቦትና አጠቃቀም**
6. **አስተዳደር**